# Frequently Asked Questions about the TPES Relocation
# ስለ TPES መዘዋወር ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ባጠቃላይ**

*ተኮማ ፓርክ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት ለምንድነው ወደ ሌላ ቦታ የሚዘዋወረው?*
*ተኮማ ፓርክ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት አዲስና ተጨማሪ ህንፃ ለመንባት ታቅዷል። ይህም ከትምህርት ቤቱ ጀርባ የሚገኘው ተንቀሳቃሽ ህንፃ ውስጥ የሚገኙትን ተማሪዎች በሙሉ አጠቃሎ ይይዛል።*

*ተኮማ ፓርክ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት (TPES) መቼ ነው የሚዘዋወረው?*
*ተኮማ ፓርክ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት በመጪው የትምህርት ዘመን 2009-2010 አሁን ካለበት ህንፃ ይዘዋወራል።*

*ተኮማ ፓርክ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት አሁን ወዳለበት ቦታ መቼ ይመለሳል?*
*ትምህርት ቤቱ በ2009-2010 የትምህርት ዘመን አሁን ወዳለበት ህንፃ ይመለሳል። ከተመለሰም በኋላ ምናልባት ጥቃቅንስራዎልች ሊከናወን ይችል ይሆናል ቢሆንም ተማሪዎች ኦገስት 2010 በአዲሱ ህንፃ ትምህርታቸውን ከመጀመር አያግዳቸውም።*

*ተኮማ ፓርክ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት ወዴት ነው የሚዘዋወረው?*
*ተኮማ ፓርክ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት ሞንት ጎመሪ ካውንቲ ቤተስዳ በሚገኘው በአድራሻ (5701 Grosvenor Lane in Bethesda, Maryland) ይዘዋወራል።*
*ትምህርት ቤቱ በ2009-2010 የትምህርት ዘመን አሁን ያለበት ህንፃ ይመለሳል። ምናልባትም ጥቃቅን ስራዎልች ሊከናወን ይችል ይሆናል ቢሆንም ተማሪዎች ኦገስት 2010 በአዲሱ ህንፃ ትምህርታቸውን ከመጀመር አያግዳቸውም።*

*ተኮማ ፓርክ ኤለመንተሪ ትምህርት ዋናው ህንፃ ይታደሳል?*
*አይታደስም ሆኖም ጥቃቅን ስራ ሊኖር ይችላል።*

*አዲሱ ህንፃ ምን ተጨማሪ ይኖረዋል?*
*አዲሱ ህንፃ ከትምህርት ቤቱ ጀርባ የሚገኘውን ተንቀሳቃሽ ህንፃ ሲተካ ተጨማሪ 16 ክፍሎች ይኖሩታል። የፕሪኬ ክፍስ ኢሶል ኮምፑተር ላብ የአስተማሪዎች ላውንጅ የካውንስለር ክፍል የመሳሰሉት ይኖራል። በተጨማሪም አዲስ የአውቶቡስ መሳፈሪያ ፊላደልፊያ አቨኑ ላይ ይኖራል።*

*አዲሱ ህንፃ ሌላ ትምህርት ቤት የሚሄዱትን የተኮማ ፓርክ ነዋሪ ተማሪዎች ለመጨመር ይችላል?*
*አዲሱ ህንፃ አሁን ካሉት ተማሪዎች (ወደ 400 ተማሪዎች) በላይ መያዝ ይችላል። የድንበር ክልል ጥናት በመካሄድ ላይ ሲገኝ በ2010 የትኛዎቹ ተማሪዎች ተጨማሪ ወደ ተኮማ ፓርክ እንደሚመጡ ይወሰናል።*

*ባለው የኢኮኖሚ አንፃር ከካውንቲው የህንፃው ግንባታ ባሉት ሰአት እንደሚያልቅ ዋስትና አለ?*
*ካውንቲው ግንባታው በሰአቱ እንደሚያልቅ አሳስበዋል። ሆኖም የተኮማ ፓርክ ወላጆች ኮንስትራክሽኑን በቅርቡ በመከታተል ሪፖርት ያቀርባሉ።*

ትምህርት ቤት የሚጀመርበትና የሚያል ሰአት አንድ ነው?
ትምህርት ቤት በ9:05 ሲጀመር በ9:05 ያልቃል።
ወላጆችና ተማሪዎች ትምህርት ቤቱን ለመጎብኘት ይችላሉ?
የተኮማ ፓርክ ፒቲኤ ወደ ትምህርት ቤቱ ፊልድ ትሪፕ በማዘጋጀት ላይ ነው። የጠለቀ ኢንፎርሜሽን ተከትሎ እንልካለን።

በትምህርት ቤቱ አካባቢ ይለው መሪት ምን ይሆናል?
የትምህርት ቤቱ ፒቲኤ ከኮንስትራክሽኑ ቲም ጋር በመተባበር የትምህርት ቤቱን ጋርደን በደንብ እንዲጠበቅ ይከታተላሉ።

የተኮማ ፓርክ ኤለመንተሪ ትምህርት ኪንደር ጋርደን ኦረንቴሽን የትና መቼ ነው የሚከናወነው?
ኪንደር ጋርደን ኦረንተሽን ኤፕሪል 23ና 24 በተኮማ ፓርክ ኤለመንተሪ ትምህርት ይከናወናል።

## ትራንስፖርቴሽን

ተማሪዎች ወደ ግሮስ ቨነር እንዴት ነው የሚጒጒዙት?
ካውንቲው ለመላው ተማሪዎች አውቶቡስ ያቀርባል።

ተማሪዎቹ አውቶቡስ የት ነው የሚያገኙት?
የሞንት ጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቤት ትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት የአውቶቢሱን መንገድ በማመቻቸት ላይ ይገኛል። ሆኖም በወቅቱ የሚገኘው የአውቶቢስ ማቆሚያ ሳይለወጥ ተጨማሪ ይኖራል። የትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንትእንደተገነዘ በው የተማሪዎች መኖሪያ ከአውቶቢስ ማቆሚያው ግማሽ ማፓይል አያልፍም። ተማሪዎችም በተመቻቸው የአውቶቢስ ማቆሚያ መጠቀም ይችላሉ። የአውቶቢስ መንገድ ስኬጁዋል በቅርቡ ይወጣል።

የአውቶቢስ ማቆሚያ የት እንደሚሆን እንዴት ነው የሚወሰነው? አንዴ ከተወሰነ ሊቀየር ይችላል?
የአውቶቢስ ማቆሚያ የሚወሰነው በአድራሻ ሲሆን ከትምህርት ቤት በፊትና በሃላ ያሉት ፕሮግራሞች ማቁሚያ ሊስቱ ላይ ሊጨመሩ ይችላሉ። የሞንት ጎመሪ ትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት ትምህርት በተከፈተ የመጀመሪያ ሁለት ሳምንት ውስጥ በመከታተል አስፈላጊ ከሆነ ለውጦችን ሊኖሩ ይችላሉ።.

የፓይኒ ብራንች ተማሪዎች በአንድ አውቶቢስ ነው የሚመላለሱት?
ለፓይኒ ብራንች ተማሪዎች የተለየ አውቶቢስ ይኖራል።

ወደ ግሮስ ቨነር መንገዱ ምን ያክል ግዜ ይወስዳል?
የሞንት ጎመሪ ትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት እንደገመተው 30 ደቂቃ መንገዱ ይወስዳል።.

ልጄ ጠዋት አውቶቢሱን በስንት ሰአት ያገኛል ሲመለስስ ስንት ሰአት ይደርሳል?
የትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት እንደገመተው ጠዋት ከ8:10 እስከ 8:30ና ከሰአት በሃላ ከ4:10 እስከ 4:30 ባለው ሰአት ውስጥ ይሆናል።

ልጄ አውቶቢሱ ካመለጠው ምን ይሆናል?
ተማሪውን ወደ ትምህርት ቤት መውሰድ የወላጅ ግዴታ ይሆናል።

አውቶቢስ መሳፈሪያው ጋር ከሌለሁ ምን ይሆናል?

ወላጆች መሳፈሪያው ጋር መገኘት ካልቻሉ ሌላ መፍትሄ የማግኘት ግዴታ አለባቸው። ፒቲኤው ለአንዳንድ አጋጣሚዎች ትብብር ተጠሪ የወላጅ ስምና ስልክ ቁጥር ለአውቶቢስ ነጂው ሲሰጥ መላው ወላጆች ተጨማሪ ስልክ ቁጥር መስጠት ይችላሉ። ፒቲኤውና የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪዎች ተቀባይ ለሌላውቸውና ብቻቸውን ለቀሩ ተማሪዎች ምን ማድረግ እንደሚቻል ፕላን ያወጣሉ ሆኖም ልጆቹን የመቀበል ግዴታ የወላጅ ነው።

ወደ ግሮስ ቨነር አውቶቢሱ በምን መንገድ ነው የሚሄደው?
የትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት በየት መንገድ እንደሚሄድ ግልፅ አላደረገም። ቤልት ዌይ አብዛኛውን ግዜ ብዙ ትራፊክ ስለሚኖር የአውቶቢስ ተቆጣጣሪዎች አመቺ የሆነውን መንገድ ይጠቀማሉ።

ከክልሉ ውጪ ላሉ ተማሪዎች የአውቶቢስ ሰርቪስ ይኖራል?
የሰአት ልዩነት ቢኖረውም ሰርቪሱ ይኖራል።

ለተማሪዎች የአውቶቢስ መንገዱ አመቺ እንዲሆን ምን ይደረጋል?
የተኮማ ፓርክ አስተማሪዎች የትምህርት ሰአቱን በማሳጠር ለተማሪዎች ትንሽ ቁርስ ለመብያና የመታጠቢ ቤት ለመጠቀም ግዜ ለመስጠት እየተወያዩ ነው።

አውቶቢሱ ውስጥ ሌላ አዋቂ ይኖራል?
ፒቲኤውና የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች ፈቃደኛ ወላጆችን የማስተባበር ፕላን እያወጡ ነው። ወላጆች ቦታ እስካለ ድረስ በአውቶቢሱ የመመላለስ ፈቃድ ከትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪዎች አግኝተዋል።

ወደ ግሮስቨነር የሚሄድ የህዝብ ትራስፖርቴሽን ምን አለ?
ከትምህርት ቤቱ አቅራቢያ ያለው ሜትሮ ስቴሽን Rockville Pike አጠገብ ሲሆን ከዊትን ወደ ግሮስቨነ ራይዶን ባስ ቁጥር 6 ይሄዳል።

ለተለያዩ ዝግጅቶች እንደ ባክቱ ስኩልና ኦፕን ሃውስ የመሳሰሉ ትራንስፖርቴሽን ይኖራል?
ትምህርት ቤቱ የተለያዩ ዝግጅቶችን ወላጆች መሳተፍ እንዲችሉ አውቶቢስ ለማመቻቸት ገንዘብ የሚገኝበትን መንገድ እየተመለደተ ነው።

ልጄ ትምህርት ቤት እያለ ቢታመምና እኔ ወደ ከትምህርት ቤቱ ልጄን የመቀበል መንገድ ከሌለኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?
ተማሪው ከታመመና ወደ ቤት የሚሄድበት መንገድ ከሌለው የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎችና አስተማሪዎች ወደቤት የሚወሰድበትን መንገድ ለማመቻቸት ዝግጁ ናቸው። እንደሁኔታውም ተማሪዎ ትምህርት በማለቂያው ሰአት ከታመመ በአውቶቢስ በደቤት ሊመለስ ይችል ይሆናል።

## ከትምህርት በፊትና በኋላ ያሉ ፕሮግራሞች

በመጪው አመት ከትምህርት በፊትና በኋላ ያሉ ፕሮግራሞች የት ይከናወናሉ?
በአሁኑ ሰአት በትምህርት ቤቱ ያሉ ፕሮግራሞች ቦታቸው ይቀየራል። YMCA ስላይጎ አቨኑ በሚገኘው በ500Urban Centerአድራሻ ይዛዛራል። ለማንኛውም ጥያቄ በስልክ ቁጥር 301-588-7720 ወይም 301-404-1435 ደውለው ማነጋገር ትችላላችሁ። ሞርገድ ዴይኬር ከትምህርት ቤት በፊትና በሃላ ፓይኒ ብራንች ትምህርት ቤት ይሆናል። ለማንኛውም ጥያቄሱዛን ሚለርን በስልክ ቁጥር 301-587-7474 ማነጋገር ትችላላችሁ። ፒቲኤውም ከትምህርት በፊትና በኋላ የልጆች ጥበቃ በግሮስ ቨነር ትምህርት ቤት የሚከናወንበትን መንገድ እየፈለገ ነው።

ልጄ ከትምህርት በፊትና በኋላ ያሉ ፕሮግራሞች ለመሳተፍ ወደ ግሮስቨነር እንዴት ይመላለሳል?
ፒቲኤውና የሞንት ጎመሪ ትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት መፍትሄ ለመፈለግ አብረው እየሰሩ ነው።

ትምህርት ቤቱ ወደቦታው ሲመለስ ከትምህርት በፊትና በኋላ ያሉ ፕሮግራሞች ተኮማ ፓርክ ባለው ቦታ ይመለሳሉ?
ከትምህርት በፊትና በኋላ ያሉ ፕሮግራሞች ወደ ተኮማፓርክ ትምህርት ቤት ይመለሳሉ። አዲሱ ትምህርት ቤትም ለመዋእለ ህፃናት አንድ ክፍል ይኖረዋል። ሌሎች መዋእለ ህፃናት የካውንቲውን ጨረታ መግባትና ለቦታም ማሸነፍ ይችላሉ።

ልጄ ትምህርት ቤት ቁርስ ይበላል። ለመጪው አመት ቁርስ በትምህርት ቤት ይሰጣል?
በመጪው አመት ቁርስ በግሮስቨነር ትምህርት ቤት ይሰጣል። *YMCA*እንደተለመደው ለተማሪዎች የሚሰጣቸውን ምግብ ያቀርባል።

**ፒቲኤ የሚያካሄደው ፕሮግራም**

በፒቲኤ ስር የሚካሄዱት ፕሮግራሞች በመጪው አመት ይካሄዳሉ?
ፒቲኤው ፕሮግራሙን ለመቀጠል ይፈልጋል ነገርግን የወላጆች ተሳትፎና ፍላጎት ይወስነዋል። ፕሮግራሙም ከቀጠለ በግሮስቨነር ትምህርት ቤት እስከ *4:30* ይሆናል። ፕሮግራሙን በፓይኒ ብራንች ትምህርት ቤት ለማከናወን አይቻልም።

ትምህርት ቤት የሚከናወነው የወላጆችና የአስተማሪ ኮንፈረንስ የት ይከናወናል?
የተኮማፓርክ አስተዳዳሪዎችና ፒቲኤው የወላጆችና የአስተማሪ ኮንፈረንስ ለማከናወን ለሁሉም ሰው አመቺ የሆነውን መፍትሄ በህብረት ፕላን እያቀዱ ነው። እንደ ባክ ቱስኩልና ኦፕን ሃውስ የመሳሰሉ ፕሮግራሞች ግን በግሮስቨነር ትምህርት ቤት ይከናወናሉ።

የፒቲኤ የምሽት ዝግጅቶች የት ይከናወናሉ?
ፒቲኤው የሚያከናውናቸውን የምሽት ዝግጅቶች በፓይኒ ብራንች ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት ኦል ፑርፐዝ ሩም ሃሙስ ሃሙስ ይካሄዳሉ። የሁለቱም ትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎችና ፒቲኤ አባሎች በህብረት የምሽት ፕሮግራሞችን ያቅዳሉ።